# የቋንቋዎች ትምህርት አስፈላጊነት

## ጌታቸው ኃይሌ

ከመጀመሪያው ልጀምር ፤ ቋንቋ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ የመገናኛ ዘዴ ነው ። እንደማንኛውም ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል ። አንድ ሰው የማሰብ ችሎታው የቱን ያህል እንደሆነ የሚመረምሩ ጠበብት ፥ "ደንቆሮ ሆኖ የተወለደ ሰው መነጋገር ለምን አይችልም?" የሚል ጥያቄ አላቸው ። ሲያድግ የሰማው ቋንቋ ስለሌለው በየትኛው ቋንቋ ይናገር? ቋንቋ አንድ ማኅበረሰብ የፈጠረው መሣሪያ ነው ። ያንን ማኅበረሰብ ነገድ ያደርገዋል ። ሌላ ቋንቋ ከሚናገር ማኅበረሰብ (ነገድ) ያርቀዋል ፤ ባዳ ያደርገዋል ። ወገን የመለያ ማስረጃ ያደርገዋል ። ተሳስቶ ዘር መለያም ያደርገዋል ።

ቋንቋ ያድጋል ፤ ይሞታልም ። የሚያድገው ብዙ አዳዲስ ነገሮች ሲፈጠሩ ለነሱ ስም በማውጣት መዝገበ ቃላቱ ሲተልቅ ነው ። አዳዲስ ነገሮች እቃዎች ብቻ አይደሉም ፤ አዳዲስ ሐሳቦችም አሉ ። "ይኸንን የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ ምን እንበለው?" እያልን የምንጠይቀው እቃን ብቻ ሳይሆን ሐሳብንም ነው ።

ቋንቋ የሚሞተው ተናጋሪዎቹ እሱን ትተው ሌሎች የሚናገሩትን ቋንቋ ሲናገሩ ነው ። የወላጆችን ቋንቋ ትቶ ሌላውን ቋንቋ መናገር በቀላሉ የሚፈጸም ሲሆን ውጤቱ ትልቅ ነገር አለው ። ሕዝብን በቋንቋ መከፋፈልን ይንደዋል ። ያ ሰው ራሱን ለጊዜው የወላጆቹ ዘር ቢያደርግም ልጆቹና የልጅ ልጆቹ ራሳቸውን የወላጆቻቸው ዘር ወይም ነገድ አያደርጉም ። በማህል ቤት ጋብቻና ፍልሰት አሉ ።

ሰዎች የራሳቸውን ቋንቋ ትተው ወደሌላው ቋንቋ የሚሄዱበት ምክንያት አላቸው ። ዋናው አካባቢው ነው ። በአንድ አካባቢ ያለው አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረው ጉራግኛ ከሆነ ፥ የአማርኛ ተናጋሪ ቤተ ሰብ ልጆች ቋንቋቸው የአካባቢው ልጆች ቋንቋ ይሆናል ። ይህ ሁኔታ ብዙ ቋንቋዎችን ገድሏል ። ዛሬ አማርኛ የሚናገሩ ሰዎች ባሉበት አካባቢ ብዙ ቋንቋዎች ይነገሩ ነበር ። ዛሬ አማርኛ ተናጋሪዎች ሆነዋል ። እንዲሁም ዛሬ ኦሮምኛ የሚናገሩ ሰዎች በሰፈሩበት አካባቢ ብዙ ቋንቋዎች ይነገሩ ነበር ። ዛሬ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ሆነዋል ። ከዚያም አልፈው እነዚህ አማሮች እነዚያ ኦሮሞዎች ሆነዋል ። አብሮ መኖር ይኸንን ለውጥ ተቀባይነት አስገኝቶለታል ። ግን ከዚያው ጋራ ተያይዞ የሚመጣ አደጋ አለ ። አንዱን ቋንቋ ክቡር ሌሎቹን ቋንቋዎች ሕሱራን (የተናቁ) የሚያደርግ አደጋ አለው ። ከዘመን ብዛት በአካባቢው የጋራ ቋንቋ የሆነውን ኦሮምኛን ወይም አማርኛን የባዳ ቋንቋ ያደርገዋል ። በተለየ አማርኛ የመንግሥትና የምሁራኑ ቋንቋ በመሆኑ ብዙዎቻችን የራሳችንን ቋንቋ ትተን አማርኛን ቋንቋችን አድርገነዋል ። ሁሉም ወደጥንት ዘመዶቹ ቋንቋ ይመለስ ቢባል ብዙዎቻችን መግቢያ እናጣለን ። አለዚያም ቋንቋችንም ነገዳችንም አማርኛ ነው ብለን እንከራከራለን ። የሆነውም ይህ ነው ።

ብዙ ቋንቋዎች እሚነገሩበት ሀገር አንዱ ቋንቋ የሁሉ መገናኛ የሚሆነው በተለመደ የታሪክ ሂደት ነው ። ሂደቱ በፈረንሳይና በጀርመን ሲፈጸም አይተናል ። ይህ የነገዶች ተጨማሪ መገናኛ መሆን ለቋንቋው ክብር

ስለሚያለብሰው ፥ ሌሎችም ምክንያት እየፈለጉ የራሳቸው ቋንቋም ብሔራዊ የመገናኛ ቋንቋ እንዲሆን ይጠይቃሉ ። ግን አንድ ቋንቋ በሀገር ደረጃ የመገናኛ ቋንቋ የሚሆንበት የራሱ "የተፈጥሮ" መንገድ ስላለው ፥ በዚያ መንገድ ያልመጣ ቋንቋ ተጨማሪነት ዕድል የለውም ። እርግጥ ፥ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩ ሕዝቦች ከቅኝ ግዛት ሲላቀቁ ፥ "በምን ቋንቋ እንጀምር" ሊሉ ይችላሉ ። ያም ቢሆን የታሪክ ሂደት ስላለበት ምርጫው ውሱን ነው ። አብዛኛውን ጊዜ በዚያው እስከዚያች ዕለት ይተዳደሩበት በነበረው ቋንቋ ይቀጥላሉ ።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ፥ ብሔራዊ ቋንቋ መሆኑን አማርኛ ቀደም ብሎ ወስዶታል ። ዛሬ ከእንግሊዝኛ በቀር የሚያሰጋው ቋንቋ የለም ። ግፋ ቢል ፥ "የኛም ቋንቋ በመንግሥት ደረጃ ተጨማሪ መጠቀሚያ ይሁን" የሚሉ ፖለቲከኞች ቢኖሡ ነው ። ይህን ዓይነት ጥያቄ ማስተናገድ ደግሞ ከታሪካዊ ሂደት ወጥቶ ሕዝብ ላይ ከባድ ጫና በግድ መጫን እንጂ ፥ ባይማሩት ቢቀር የማይጐዳ ቋንቋ ለማስተማር በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም ። ቋንቋ የመገናኛ መሣሪያ ከሆነ ሁለተኛ ቋንቋ መማርና ማስተማር ጊዜና ሀብት ማባከን ነው ። ቋንቋም እንደ ልብስ የዘወትርና ለበዓል የሚሆን ሌላ የክት ቋንቋ ቢያስፈልግ ተጨማሪ ቋንቋ እንማር ነበር ። የተናጋሪውን ሕዝብ ብዛት ምክንያት የሚያደርጉ አሉ ፤ አያስኬድም ። አንድ ሰው እንኳን ተናጋሪ የሌለው ግዕዝ የኢትዮጵያ የጽፈት ቋንቋ በመሆን ለዘመናት አገልግሏል ። አንድ ሰው እንኳን ተናጋሪ የሌለው እንግሊዝኛ የኢትዮጵያ ተጨማሪ ቋንቋ በመሆን እያገለገለ ነው ። ለመገናኛ የማያስፈልግ ቋንቋን "ተናጋሪዎቹን ለማስደሰት እንማረው" አይባልም ። ልብስ የምንገዛው ዕርቃናችንን ለመሸፈን ፥ ከብርድ ጥቃት ለመዳን እንጂ ፥ ሸማኔውን ለማስደሰት ወይም ልብሱ የሚገዛው አጥቶ ስላሳዘነን አይደለም ።

በቅርብ ጊዜ ያነበብኩት ሌላ ምክንያት አለ ፤ በየክልሉ ትምህርት ቤቶች ሦስት ቋንቋዎች (1. የክልሉ ቋንቋ ፥ 2. አማርኛ ፥ 3. እንግሊዝኛ) ሲሰጡ በአማራው ክልል የሚሰጡት ቋንቋዎች ሁለት (1. አማርኛና 2. እንግሊዝኛ) ብቻ ስለሆኑ ፥ እዚህም የሚሰጡት ቋንቋዎች እንደሌሎቹ ክልሎች ሦስት እንዲሆኑ ኦሮምኛ ይጨመርላቸው የሚል ነው ። ይኸንን ምክንያት የሚያደርጉ ፖለቲከኞች በየክልሉ ሦስት ቋንቋዎች ሲሰጡ በአማራው ክልል ሁለት ቋንቋ ብቻ የሚሰጥበትን ምክንያት ያዩት አይመስለኝም ። ክልሎች በራሳቸው ቋንቋ ላይ እንግሊዝኛ የሚማሩት የዓለም-አቀፍ ቋንቋ ስለሆነ ፥ አማርኛ የሚማሩት ብሔራዊ ቋንቋ ስለሆነ ነው ። "ኦሮምኛን በተጨማሪ በአማራው ክልል እናስተምር" ካልን ፥ ተጨማሪ ቋንቋዎች በሌሎቹ ክልሎች ለማስተማር ከተሰጠው ምክንያት ወጥተን ሌላ ምክንያት መፈለግ ሊኖርብን ነው ። ያ ሌላ ምክንያት ምንድ ሊሆን ነው? ሦስት እንዲሞላ ከተባለ ፥ ቋንቋ ማስተማር ከቁጥር ሦስት ፥ ማለት ከሥላሴ ፥ ጋር ግንኙነት የለውም ። ሦስት የመጣው ሁኔታው አስገድዶ ነው ። "አማሮቹ ተጨማሪ ቋንቋ መማር ቀረባቸው" ተብሎ ታዝኖላቸው ከሆነና እነሱም ሐዘኑ ከተሰማቸው የትኛውን ቋንቋ እንደሚማሩ ምርጫው የነሱ ይሁን ። አጠገባቸው ሌሎች ቋንቋዎች ስላሉ ፥ ምናልባት ከነሱ ውስጥ የሚጠቅማቸውን ቋንቋ ይመርጡ ይሆናል ። ኦሮምኛንም ሊመርጡ ይችላሉ ። ግን ቋንቋ የመገናኛ ዘዴ ከሆነ ፥ ሁላችንም በክልል ታጥረን ሳለ ፥ አማሮቹ ኦሮምኛ ቢማሩ ፥ አማርኛ ከማያውቁ ኦሮሞዎች ጋር የት ተገናኝተው ነው

የሚነጋገሩበት? ቋንቋ እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚቻለው መጀመሪያ ክልሎቹን በማፍረስ ፥ ከላሊዎቹን በመደምሰስ ነው ። ካየሁት ልናገርና ፥ የሸዋ ሰዎች ብዙዎቻችን ቋንቋችን አማርኛና ኦሮምኛ ነው ። ታዝዘን ሳይሆን አስፈልጎን የምናደርገው ነው ።

በዛሬው ፖለቲካ ፥ አማሮች ሁለት ቋንቋ ብቻ የሚማሩበትን ታሪካዊ ምክንያት ብዙ ሰው አያውቅም ። ታሪኩ እንዲህ ነው ፤ የራሳቸውን የጎሳ ቋንቋ (አገውኛን ፥ ቅማንትኛን ፥ ወዘተ.) ከዘመን ብዛት ትተው አማርኛን የጎሳ ቋንቋቸው ስላደረጉት ነው ። የጎሳ ቋንቋቸውን አልተዉት ቢሆን ኖሮ ዛሬ ሦስት ቋንቋዎች ይማሩ ነበር ። በየሌሎች ክልሎችም ሁለት ቋንቋ ብቻ ለመማር ከፈለጉ በአማራው ክልል ውስጥ ያሉ ጎሳዎች እንዳደረጉት ሊያደርጉ ይችላሉ ። ወያኔዎች መጥተው አደናቀፉት እንጂ ፥ ማድረግም ጀምረው ነበር ። ቋንቋ በመማር የመንግሥት እጅ ከገባበት እጅ እጅ ይላል ። አማርኛ በመንግሥት ቋንቋነት በሰላም በሁሉ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ሳለ ፥ ያስፈራራው ያለ ይመስል ፥ "የመንግሥቱ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል" የሚል ሕግ ተደነገገ ፤ ሳይቸግር ጤፍ ብድር ። በዚህ ጊዜ ነው ፥ ሌሎች "የኛ ቋንቋስ" ማለት የጀመሩት ።

ሆኖም ፥ ሌሎች ቋንቋዎች በከፍተኛ ደረጃ ለመማር ሦስት ምክንያቶች አሉ ፤ አንደኛው የቋንቋው ሥነ ጽሑፍ ነው ። ብዙ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ፈረንሳይኛ ፥ ጀርመንኛ ፥ ረሽኛ ፥ ያስተምራሉ ። የእነዚህ ቋንቋዎችን ሥነ ጽሑፍ ለማወቅ የሚፈልጉ ብዙ ተማሪዎች አሉ ። ግዕዝንም ያካበተውን ዕውቀት ለማግኘት  የሚማሩት አሉ ። ትርፍ ቋንቋ የመማር አስፈላጊነት አንዱ ምክንያት ይኸ ነው ።

ሁለተኛው ምክንያት በየቋንቋው ያሉ ተረቶችና የአፍ ታሪኮች በዚያው ቋንቋ ሊጠኑና ወደ ሌሎች ቋንቋዎች ሊተረጐሙ የሚገባቸው መሆኑ ነው ። በየቋንቋው ያሉ ተረቶችና ምሳሌዎች ፍልስፍና አዝለዋል ። መታወቅ አለባቸው ።

ሦስተኛው ምክንያት የቋንቋ ተመራማሪዎችን ይመለከታል ። እነዚህ ባለሙያዎች እንደሚሉት እያንዳንዱ ቋንቋ ሊታወቅ ሊመረመር የሚገባው አወቃቀር አለው ። የሰው አካል አወቃቀር እንደሚመረመር የቋንቋ አወቃቀርም ይመረመራል ። ለምሳሌ ፥ ዳዊት ውስጥ እንዲህ የሚል አረፍተ ነገር አለ ፤

የፀቅብ ሕፃናተ እግዚአብሔር።

ይጠብቃል ሕፃናትን እግዚአብሔር።

ግዕዙ ከግራ ወደቀኝ የሄደውን አማርኛ ከቀኝ ወደግራ ሄደው ።

ብዙ ምሳሌዎች ለመስጠት ቦታው አይደለም ። ዋናው ቁም ነገር ቋንቋን የሰው አእምሮ እንዴት እንዳነጸው መታወቅ እንዳለበት ይታመናል ። ቋንቋዎች አደጋ ላይ እንዳሉ ዘሮች (እንደ endangered species) ልንከባከባቸው ይገባላል ።

አንድ ቋንቋ በመጻፍ መጠቀሚያ እንዲሆን ከተወሰነ ፥ የሚቀጥለው ጥያቄ "በምን ፊደል ይጻፍ?" የሚለው ይሆናል ። እስከዛሬ እንዳየነው ፥ የተፈጥሮ ወሳኙ ጉርብትና ወይም ሃይማኖት ነበር ። የጐረቤት  ወይም

የራስ ሃይማኖት የተጻፈበት ቋንቋ **ሳይመረጥ ዐውቆ ይመረጣል ።** “ሳይመረጥ ዐውቆ ይመረጣል” ማለት “የታሪክ ፥ የተፈጥሮ ሂደት ነው” ማለት ነው ። “በምን ፊደል ይጻፍ” ማለት በውሳኔው የሰው እጅ ማስገባት ስለሆነ ፥ መወሰኑ የተጠቃሚዎቹ መብት ይሆናል ። ለምሳሌ ፥ ኦሮምኛን መላ የኢትዮጵያ ልጆች እንዲማሩት በበቂ ምክንያት ከተወሰነ ፥ ልጆቹ በለመዱት ፥ በተፈተነው ፥ በቆንጆው የኢትዮጵያ ፊደል መጻፍ አለበት ። ትምህርቱም ከሰሜን ከትግራይ ጀምሮ እደቡብ ድረስ መሰጠት አለበት ። “የሚፈለገው የኦሮሞ ልጆች ብቻ እንዲጽፉት ነው” ከተባለና በሙያዬ ምክንያት እንዳማክር ካልተጠየኩ ፥ የኦሮሞ ነገድ በፈለገው ፊደል ቢጽፈው መብቱ ነው ። ሆኖም ፥ በሀገር በቀሉ በኢትዮጵያፊደል መጻፋቸውን ትተው ያለ በቂ ምክንያ በሌላ አገር ፊደል ከጻፉ ግን ሌላ የጥላቻ ሐውልት ማቆማቸው እንዳይሆን እሰጋለሁ ።